መልእክት ሦስት

## የእግዚአብሔር መሠዊያ—
## የሚቃጠለው መሥዋዕት መሠዊያ—መልሶ መሥራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘሌ. 1፡3-11፣ 13-14፤ 17፤ 6፡9፣ 12፣ 13፤ ዘኍ. 28፡2፤
ዕዝ. 1፡2-3፣ 5፤ 3፡2-3፣ 6፤ መዝ. 43፡4፤ ኤፌ. 5፡2፤ ሮሜ 12፡1

**I. "በእግዚአብሔር ሰው በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያቀርቡበት ዘንድ የእስራኤልን አምላክ መሠዊያ ሠሩ—ዕዝ. 3፡2፦**

ሀ. ለቤቱ ምለሳ የመሠዊያው ምለሳ ያስፈልገናል—1፡2-3፣ 5፤ 3፡2-3፦

1. ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት መመለስ ያለበት የመጀመሪያው ነገር መሠዊያው ነው—ሮሜ 12፡1፦
   - ሀ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሊኖረን ከመቻሉ በፊት፣ ሁሉንም ነገር በመሠዊያው ላይ ማስቀመጥ አለብን—መዝ. 43፡4።
   - ለ. ያለንን ሁሉ፣ የሆንነውን ሁሉ እና ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እርካታ በመሠዊያው ላይ ማስቀመጥ አለብን፤ ይህ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጅማሬ ነው።
2. ችግሩ፣ የተመለስነው ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መሆኑ ነው፣ ሆኖም ግን በኢየሩሳሌም አሁንም ብዙ ነገሮችን ለራሳችን ፍላጎቶች ልናስቀምጥ እንችላለን፤ ለእግዚአብሔር ፍላጎቶች እና ለእግዚአብሔር እርካታ ሁሉን ነገር በመሠዊያው ላይ ላናቀርብ እንችላለን—ሮሜ 12፡1፦
   - ሀ. ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ሆኖም ግን ሕይወታችንን በባቢሎን እንደነበር መቀጠል የለብንም።
   - ለ. በኢየሩሳሌም ያለው ሕይወት ፈጽሞ ለጌታ ፍላጎቶች መሆን አለበት።

ለ. የሚቃጠለው መሥዋዕት መሠዊያ የክርስቶስን መስቀል በምሳሌ ያሳያል—ዘጸ. 27፡1፤ 40፡6፤ ዕብ. 13፡10፦

1. በኢኮኖሚው እግዚአብሔር አንድ ማንነት—ክርስቶስን—እና አንድ መንገድ—መስቀሉን ይሰጠናል—1 ቆሮ. 2፡2፦
   - ሀ. መስቀሉ በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር አሠራር ማዕከል ነው—ገላ. 1፡4፤ 2፡19-21፤ 3፡1፣ 13፤ 5፡24፤ 6፡14።
   - ለ. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በመስቀሉ ይገዛል፣ ሁሉንም ነገር በመስቀሉ ያስተካክላል—ቆላ. 1፡20-22፤ 2፡11-15።
2. መስቀሉ የመንፈሳዊ ልምምዶች ሁሉ መሠረት፣ መነሻ ነው፤ ሁሉም መንፈሳዊ ልምምድ ከመስቀሉ ይጀምራል—ገላ. 2፡20፤ 6፡14፤ 1 ቆሮ. 2፡2፦
   - ሀ. በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመገስገስ፣ በየዕለቱ በመስቀሉ ማለፍ ያስፈልገናል—ማቴ. 10፡38፤ 16፡24፤ ሉቃ. 14፡27።
   - ለ. ተገቢ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዲኖረን ከፈለግን፣ መስቀሉን መለማመድ ያስፈልገናል—ኤፌ. 2፡14-16።
   - ሐ. በመስቀሉ ምንም መሆን፣ ምንም የሌለን መሆን፣ ምንም ማድረግ የማንችል መሆን ያስፈልገናል፤ አለበለዚያ፣ የሆንነው፣ ያለን እና ማድረግ የምንችለው ነገር የክርስቶስ ምትክ ይሆናል—1 ቆሮ. 1፡17-18፣ 23።

**II. "ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ጀመሩ"—ዕዝ. 3፡6፦**

ሀ. የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስ ፍጹም ለእግዚአብሔር እርካታ መሆኑን ያመለክታል—ዘሌ. 1፡3-9፦

1. ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እርካታ የነበረው የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር ደስታ እና እርካታ በምሳሌ ያሳያል—ኤፌ. 5፡2።
2. የሚቃጠለው መሥዋዕት በምሳሌ የሚያሳየው ክርስቶስን ፍጹም እና ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሆነ ሕይወትን በመኖሩ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲህ ያለው ኑሮ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሕይወት በመሆኑም ጭምር ነው—ዮሐ. 5፡19፣ 30፤ 6፡38፤ 7፡18፤ 8፡29፤ 14፡24፤ 2 ቆሮ. 5፡15፤ ገላ. 2፡19-21።
3. የሚቃጠለው መሥዋዕት ክርስቶስ ራሱ ነው፣ እኛም ከእርሱ ጋር አንድ ነን፤ ስለዚህ፣ የሚቃጠለው መሥዋዕት ከክርስቶስ ጋር አንድነታችንም ነው—1 ቆሮ. 6፡17።

ለ. የሚቃጠለው መሥዋዕት እግዚአብሔር እንዲደሰተው እና እንዲረካ ለእግዚአብሔር ምግብ ነው—ዘኁ. 28፡2፦

1. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ቢሆንም፣ የሚበላውን ነገር ለራሱ ማቅረብ አይችልም፤ ምግቡ ከሕዝቡ መምጣት አለበት—ቁ. 2።

2. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምግብ ነው፣ ነገር ግን እርሱ በቀጥተኛ መንገድ የእግዚአብሔር ምግብ አይደለም፤ ይልቁንም፣ ክርስቶስ በእኛ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የእግዚአብሔር ምግብ ነው።

ሐ. "የሚቃጠል *መሥዋዕት*" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል በቀጥታ ሲተረጎም "ወደ ላይ የሚወጣ" ማለት ነው፣ ይህም ወደ እግዚአብሔር የሚዐርግ ነገርን ያመለክታል፤ ይህ ዕርገት ክርስቶስን ያመለክታል—ዘሌ. 1፡3፣ 10፣ 14፦

1. ከምድር ወደ እግዚአብሔር ማረግ የሚችለው ብቸኛው ነገር በክርስቶስ የተኖረው ሕይወት ነው፣ ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የሆነ ሕይወትን የኖረው ልዩና ብቸኛ ማንነት እርሱ ነውና—ዮሐ. 6፡38።
   ሀ. ክርስቶስ እንደሚቃጠለው *መሥዋዕታችን* ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር፣ ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ነው—4፡34፤ 5፡30፤ ዕብ. 10፡8-10።
   ለ. ጌታ ኢየሱስ የሆነው የትኛውም ነገር፣ የተናገረው የትኛውም ነገር እና ያደረገው የትኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ነበር—ዮሐ. 6፡38፤ 5፡17፣ 36፣ 45፤ 8፡28፤ 10፡25፤ 12፡49-50።
2. እንደ ሚቃጠለው *መሥዋዕት* በክርስቶስ ላይ እጆቻችንን በመጫን፣ ከእርሱ ጋር እንጋጠማለን—ዘሌ. 1፡4፤ 1 ቆሮ. 6፡17።
3. ክርስቶስ በእኛ ሲኖር፣ በምድር ላይ የኖረውን ሕይወት፣ የሚቃጠለውን *መሥዋዕት* ሕይወት በእኛ ይደግመዋል—ገላ. 2፡20።

መ. የሚቃጠለው *መሥዋዕት* "በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ" ነው—ዘሌ. 1፡9፣ 13፣ 17፦

1. "ጣፋጭ ሽታ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል በቀጥታ ሲተረጎም "የእረፍት ወይም የእርካታ ሽታ" ማለት ነው—ቁ. 9።
2. የሚያረካው ሽታ እርካታን፣ ሰላምን እና እረፍትን የሚያመጣ ሽታ ነው፤ እንዲህ ያለው የሚያረካ ሽታ በእግዚአብሔር ዘንድ ድሰታ ነው።
3. ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እርካታ የሆነ ሕይወት ስለኖረ፣ ኑሮው ለእግዚአብሔር ደስታ እና እርካታ የሚዐርግ የሚያረካ ሽታ፣ ጣፋጭ ሽታ ነበር—ኤፌ. 5፡2።

## III. በዘሌዋውያን *መጀመሪያ* የተጠቀሰው *መሥዋዕት* የኃጢአት *መሥዋዕት* ወይም የበደል *መሥዋዕት* ሳይሆን የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ነው—1፡3፦

ሀ. ክርስቶስ *መጀመሪያ* እንደ ሚቃጠለው *መሥዋዕት* የሚያስፈልገን በእግዚአብሔር ፊት ያለን የመጀመሪያው ሁኔታችን፣ ከእግዚአብሔር ጋር በተገናኘ የመጀመሪያው ችግራችን የመተላለፍ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ያለመሆናችን ጉዳይ ስለሆነ ነው፦

1. እግዚአብሔር መገለጡ እና መወከሉ እንድንሆን ፈጠረን—ዘፍ. 1፡26።
2. እግዚአብሔር ለእርሱ እንሆን ዘንድ ፈጠረን፤ ለራሳችን አልፈጠረንም፣ ነገር ግን እንደ ወደቁ ሰዎች፣ የምንኖረው ለእርሱ ሳይሆን ለራሳችን ነው።

ለ. የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ማለት እግዚአብሔርን ለመግለጥ እና ለመወከል ዓላማ በእግዚአብሔር እንደተፈጠሩ ሰዎች፣ ከእግዚአብሔር ሌላ ለምንም ነገር መሆን የለብንም ማለት ነው—ቁ. 27-28፤ ተዛ. መዝ፣ 7፡25፤ ማር. 12፡30።

ሐ. ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንዳልሆንን እና ከራሳችን ፍጹም መሆን እንደማንችል መገንዘብ ያስፈልገናል፤ ስለዚህ፣ ክርስቶስን እንደሚቃጠለው *መሥዋዕታችን* መውሰድ ያስፈልገናል—ዘሌ. 1፡3-4።

## IV. ለዘወትር የሚቃጠለውን *መሥዋዕት* ሕይወት መኖር ሕያው *መሥዋዕት* መሆን ማለት ነው—ሮሜ 12፡1፦

ሀ. የሚቃጠለው *መሥዋዕት* የመሰጠታችን፣ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንደ ሕያው *መሥዋዕት* የማቅረባችን ምሳሌ ነው፤ የመስጠት ትርጉም ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንደ ሕያው *መሥዋዕት* ማቅረብ ነው—ዘሌ. 1፡3-4፣ 8-9፤ 6፡9፣ 12፣ 13፤ ሮሜ 12፡1።

ለ. በብሉይ ኪዳን ለዘወትር የሚቃጠለው *መሥዋዕት* በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የሆንን እኛ ራሳችንን በየዕለቱ ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንዳለብን በምሳሌ ያሳያል—ዘኁ. 28፡3-8።

ሐ. ዛሬ በክርስቲያን ሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን ለዘወትር የሚቃጠለው *መሥዋዕት* አስፈላጊነት አለ—ዘሌ. 1፡3-4፣ 8-9፤ 6፡9፣ 12፣ 13።

## V. *መሻቱን* እንዲፈጽም ለእግዚአብሔር እርካታ እግዚአብሔር አብን በክርስቶስ እንደሚቃጠለው *መሥዋዕት* ማምለክ ያስፈልገናል—1፡3፣ 9፤ ዘኁ. 28፡2፤ ዮሐ. 4፡23-24፦

ሀ. እግዚአብሔር እንደ *መሥዋዕቶቹ* ሁሉ እውነታ በክርስቶስ እንድናመልከው ይፈልጋል፤ *መሥዋዕቶቹ* እግዚአብሔርን ለማስደሰት ናቸው—ቁ. 23-24።

ለ. ተገቢ አምልኮ በክርስቶስ እንደሚቃጠለው *መሥዋዕት* እግዚአብሔርን የማርካት ጉዳይ ነው—1 ጴጥ. 2፡5፤ ዮሐ. 4፡34፤ 5፡30፤ 8፡29፦

1. አብን በክርስቶስ እንደሚቃጠለው *መሥዋዕት* እውነታ ስናመልከው፣ ለእርካታው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሽታ ወደ እርሱ ያርግለታል—ዘሌ. 1፡9፤ ዮሐ. 4፡23-24።
2. ክርስቶስን እንደሚቃጠለው *መሥዋዕት* እውነታ በማቅረባችን እግዚአብሔር ስለሚረካ፣ ጣፋጭ ቅበላውን ይሰጠናል፤ የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ትርጉም ይህ ነው—ዘኁ. 28፡2።

*© 2022 Living Stream Ministry*